# ጥቂቶች ቆራጦች፤ ያልተንበረከክነው፤ ነገ እልፍ እንሆናለን፤ ታሪክ ምስክር ነው!!

በታዘቢ ይናገር 01-30-17

ይህ ዘመን ተሻጋሪ የኢህዴን/ብአዴን መስራቾች መርህ ህያው ሆኖ እንዲቀጥል በአንድ ራስ ሁለት ምላስ የተሸከሙት እና የቅብብሎሹን ዱላ ጥለው ለጠላት አስተሳሰብ ፤አላማና ተግባር የተማረኩትን ማጋለጥና መታገል ለነገ ሊባል የማይገባው ተግባር መሆኑ ወቅታዊ የሀገራችን ሁኔታ በፅሞና ለሚከታተልና ለሚገመግም እንዲሁም ጤነኛ አእምሮ ላለው ኢትዮጵያዊ ሁሉ የግድ የሚለን ደረጃ ላይ መድረሳችን ይገነዘባል ብየ አምናለሁ፡፡ ምክንያቱም በታሪካችን አይተነው የማናቀውን ሀገርን ሊበትን የሚችል ሁከትና ብጥብጥ በጎንደር፤ በባህርዳር ዙሪያ እና ሌሎችም የሀገራችን አከባቢዎች አይተናልና፡፡ በተለይም ደግሞ በጎንደር ተከስቶ የነበረው ችግር ፤ያለምንም ማጋነን ሰላም ወዳዱ የጎንደርና የትግራይ ህዝብ እንዲሁም አርቆ አሳቢ ጥቂት የፌደራል እና የሁለቱም ክልልች አመራሮች ከፍተኛ ጥረት አማካኝነት ባይበርድ ኑሮ በአለም ታይቶ የማይታወቅ እልቂት ሊከሰት ይችል እንደነበር መገመት የሚከብድ አይደለም፡፡ እነ የትም ፍጭው (እነ እውነቱ ደፈጠጠ) ግን በክልሎች በሚፈጠር ጫና አዲስ አበባ ቁጭ ብለው ስልጣን የሚገኝ መስሏቸው ነበር መሰል አዲስ አባባ ለታክሲና ለዳቦ ይሰለፋል ጎንደርና ባህርዳር ግን ለሙብቱ እንደ 1997 ይሰለፋል እያሉ የፅፉ ነበር ፡፡

በመሆኑም ሁላችንም ለሀገራችን ህዝቦች ሰላምና ብልፅግና ስንል አንዳችን ከአንዳችን ነጣጥለው እርስ በርስ እንድንተላለቅ እና የእስትራተጂክ ጠላቶቻችን መጫወቻ እንድንሆን  ቀን ተሌት የሚባዝኑትን የትም ፍጭው ዱቄቱን አምጭው አይነት መርህ የሚከተሉ በሀገር እና በህዝቡ ላይ የፈለገ ያህል ጉዳት ቢደርስም ደንታ የሌላቸው  በስልጣን ጥም የተቃጠሉትን ግለሰቦች አገር እንዳያቃጥሉ አሁንም ማጋለጥና መታገል የግድ ይለናል፡፡

እነዚህ ሀይሎች በማወቅም ይሁን ባለማወቅ የተለያዩ ማህበራዊ ሚድያዎችን በመጠቀም የሚያካሂዱትን ዘመቻ መመከት ሲቻል ብቻ ነው ጥቂቶች ግን ደግሞ ቆራጦቹ ነብስና ስጋቸው ለህዝቡ አላማ ሰጥተው የኢህዴን/ብአዴን መስራች ታጋዮች መርህ የሆነውን ጥቂቶች ቆራጦች ያልተንበረከክነው ነገ እልፍ እንሆናለን ታሪክ ምስክር ነው!! እንዲሁም ታላቁ መሪ መለስ ዜናዊ  የኛ ትግል የዱላ ቅብብሎሽ ነው ያሉትን መርህ ለማስቀጠል የቅብብሎሹን ዱላ በተጨባጭ የጣሉ ነገር ግን ደግሞ በአንድ ራስ ሁለት ምላስ እንዲሉ አለሁ አለሁ የሚሉትን አደናጋሪዎች አንዱን ምላስ ብቻ እንዲይዙ ለማስቻል ሁሉም ሊያግዛቸው ወይም ሊታገላቸው ይገባል፡፡

ስለሆነም እንዴ !!! እነዚህ ሰዎች፤ ይህ ሰው ፤ ይህች ሰው ወዘተ ምን ነካቸው እያሉ መቆዘም ወይም ዝም ማለት በአንገታችን ላይ ገመድ ሲገባ ዝም ብሎ እንደማየት ነውና ዝምታውን በመስበር የታዘብነውን፤ ያየነውን የሰማነውን እና እውነቱን በማጋለጥ ውሸታሞችን ከተግባራቸው እንዲታቀቡ ትግላችን መቀጠል የግድ ይላል፡፡

ባለፈው ፅሁፎቼ ( እንዳልፉት የለ፤ ያ ! ሁሉ ታለፈ አሁን ግን በነ እውነቱ ዘለቀ ተደፈጠጠ እና ህዝብና አገር እንዳይቃጠል ውሸታሞችና አስመሳዮችን መታገሉ ይቀጥላል በሚሉ ርእሶች)  አቶ እውነቱ ደፈጠጠ በተደጋጋሚ ስለሚፅፋቸው አደገኛ ፅሁፎች

መሰረት አድርጌ መልስ መፃፌ ይታወሳል፡፡ በዚሁ በሁለተኛ ፅሁፌ እኔ አበቃሁኝ ተማርበት ካልሆነ ግን አላርፍ ያለች ጣት --- ብየ ነበር ያበቃሁት፡፡ ሆኖም ግን በሱ ላይ ያቀረብኳቸው ሀሳቦች ጥሬ ሀቆች ስለነበሩ ምንም ሳይል በደፈናው የታዛቢ ፅሁፍ የጥላቻ ይመስላል ብሎ ለማለፍ የሞከረ ቢሆንም ሲያጠቃልል ግን ያቀረብኳቸው ሀሳቦች ትክክል መሆናቸውን አምኗል ምክንያቱም ሲያጠቃልል እውነተኛ ማንነትህ ሲታወቅ ግን ያንተም ጉድ ይወጣል በማለት ነው ያጠቃለለው ይህ ማለት በሱ ላይ የተገለፁት ጉዶች ትክክል ናቸው እያለን ነው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ የአቶ እውነቱ ደፈጠጠ እምነት እከክልኝ ልከክልህ አይነት ብታርፍ ይሻልሀል ካልሆነ ግን ያንተም ጉድ ይወጣል፡፡ እንዲህ ናት እንግዲህ ለሀቅ መቆም፡፡ ውሸታሞችንና፤ አስመሳዮችን እማ ምህረት አያስፈልግም ፤ መዋሸታቸው፤ በህዝብ ስቃይ መደሰትና  መቀለድ እስካላቆሙ ድረስ እንቀጥላለን እንጂ ገና መቼ ተነካና ወደ ትክክለኛው መስመር ከተመለሱ ግን ታሪክ ነው ብለን እንተዋልን ካልሆነ ግን ህዝቡ በሀሰት መወናበድ ስለማይገባው እንቀጥላለን፡፡

አንባቢዎች እንዲረዱልን የምፈልገው ነገር ቢኖር እነ እውነቱ ደፈጠጠ የዱላ ቅብብሎሹን ጥለው ከትግራይ ህዝብ ጠላቶች (ኢሳትና የግንቦት ሰባት) ጋር በመወገን ህዝቡ ጥቃት እንዲደርስበት በሚችሉት ሁሉ እየሰሩ በመሆናቸው እና ህወሐትና የትግራይ ህዝብን የጎዱ እየመሰላቸው ብአዴንና የአማራ ህዝብንም ጭምር በእጅጉ እየጎዱ በመሆናቸውና አገራችንን ለጠላቶቻችን ሲሳይ ለማድረግ እየተንቀሳቀሱ በመሆናቸው እንጂ በግል ጠብ የሌለኝ መሆኔን በማስረገጥ ወደተነሳሁበት ልመለስ፡፡

ይህ እውነት እየደፈጠጠ ያለው ሰው በጎንደር ስለተከሰተው ሁከትና በትግራይ ተወላጆች ላይ የደረሰው ግፍና በደል እጅግ በማቃለል ምን አዲስ ነገር ተገኝቶ ነው አፋርና ሶማሊ ክልሎች ውሱን በጀታቸውን በመቀነስ መቀሌ ይዘው ሄደው የሰጡት ብሎ በጣም በበሽቀ አንጀቱ የገለፀውን ፅሁፍ እና ከዚህ በፊት የተፃፉትን ፅሁፎች በማየትና በማመሳሰል እንዲሁም ፀሀፊው በትግረኛ በተፃፉት አርቲክሎች ሳይቀር የሰጣቸውን ሂሶች እና ሀሳቦች በማየት ማንነቱ ለማወቅ ብዙም ከባድ አልነበረም በቀላሉ ነው የተረዳሁት፡፡ ስለሆነም ከዚህ በፊት እንዳልኩት የበረሀ ስም ስላልነበረው አሁን ራሱ ባወጣው የበረሀ ስም ትንሽ በማሻሻል እውነቱ ደፈጠጠ እያልኩኝ እቀጥላለሁ፡፡

አቶ እውነቱ ደፈጠጠ በ15/12/2016 በፃፈው ላይ እንዲህ ይለናል --------(ተፈናቀሉ የተባሉት ግን በትግራይ ክልል መንግስት በቀረበው ሪፖርት መሰረት ከአምስት ሽህ አይበልጡም፡፡
ይህም ቢሆን ተገቢ ነው የሚል የመከራከሪያ ሀሳብ የለኝም፡፡ ሆኖም እውነታው ተጋኖ የሚነገርለትን ያህል ካለመሆኑም በላይ ቀደም ሲል በአርባጉጉና በመሳሰሉት የኦሮሚያ አካባቢዎች የተፈጸመውን ግፍና በደል ትተን ባለፉት አስራ አምስት አመታት ብቻ በአስር ሽዎች የሚቆጠሩ አማሮች ከኦሮሚያ ክልል በተለይም ምስራቅ ወለጋ አካባቢ፣ ደቡብ ክልል ጉራፈርዳ ወረዳ ውስጥ እና ቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል ለዘመናት ይኖሩ የነበሩ አማሮች ንብረታቸው ሜዳ ላይ ተበትኖና ወድሞ፣ ቤታቸው ፈርሶ የተወሰኑት ደግሞ አካላቸው ጎድሎና ህይወታቸው ጠፍቶ በህይወት የተረፉት በግፍ ሲፈናቀሉ የአማራ ክልል መሪዎችን ጨምሮ አንድም የክልል መንግስት ወይም የፌዴራል ባለስልጣን ድምጹን ባላሰማበት ሁኔታ አሁን ምን አዲስ ነገር ተገኝና ነው የኢትዮጵያ ሶማሊና የአፋር ክልል መንግስታት መሪዎች ውስን የሆነውን በጀታቸውን አጥፈው እያንጓንዳቸው የአስር ሚሊዮን ብር ለመስጠት ቃል መግባታቸውን በሚዲያ ሲናገሩ የቀደማቸው ሰው ያልተገኘውና ቀጥለውም ቼኩን በማስያዝ የሀገር ሽማግሌዎችን በሩጫ ወደ መቀሌ በመላክ አይዟችሁ ከጎናችሁ ነን ያሉት?).

እንግዲህ እነ አውነቱ ደፈጠጠ  ምን ያህል የፀረ ህዝቦች አጀንዳ አራማጅ እንደሆኑ ከላይ የተገፀው  ቃል በቃል ወሰደን ብንመለከት ምን እንደሚያመላክት ግልፅ ነው፤

- በመጀመሪያ ደረጃ በውስጣቸው ምንም አይነት ህዝባዊነት የሚባል እንደሌላቸው የሚያሳየው እንዱ ተፈናቀሉ የተባሉት ከአምስት ሺ ስለማይበልጡ ለምን ተጋኖ ይነገራል ይላሉ፤ እረ ሰውየ በህግ አምላክ የሰው ቁጥር እኮ ነው አምስት ሺ ብር አይደለም። ይህ ሀሳብ ከዚህ በፊትም ሰለ ሀውዜን ጭፍጨፋ አስተያየታቸውን ሲገልፁ ምን አዲስ ነገር አለው እነ ሰቆጣስ ተደብድበው የለም እንዴ እንዳሉት ኤነት ነው።

- ሌላኛው የአፋርና የሶማሌ ክልል ድጋፍ አደረጉ ህዝባዊነት፤ መተጋገዝ ማለት እንዲህ ነው ፤ እኛስ ምን እናግዝ ማለት ሲገባቸው ምን አዲስ ነገር ተገኝቶ ነው ብለውን እርፍ። ወይ ህዝባዊነት ፤ ወይ ከህዝብ በፊት እኔ ልሙት። ለነገሩ ህዝባዊነት ምን እንደሆነ ስለማያቁት አይፈረድባቸውም። ማንነታቸው ባለፈው ፅሁፌ (እንዳያልፉት የለ! ያ ! ሁሉ ታለፈ አሁን ግን በእነ እውነቱ ደፍጥጥ ተደፈጠጠ) በደምብ ስለተብራራ ብዙም ተጨማሪ አያስፈልገውም ያስፈልጋል ከተባለ ግን የኢንፎርሜሽን እጥረት እንደሌለ ላረጋግጥላቸው እወዳለሁ።

- እላይ ከተገለፁት ውጭ ግን የጎንደርና እና ከማእከል ይሁን ከክልል ከተሞች እጅግ በጣም እሩቅ በሆኑ አከባቢዎች በአማራውና በሌላውም በመርህ አልባ እንደ እነ አውነቱ ደፈጠጠ አይነቱ ሰዎች የበላይነት በያዙባቸው ቦታዎች እንዲሁም በግንዛቤ ደረጃ በጣም ያልተማሩ አከባቢዎች የተፈፀሙ ጥቃቶች ለማመሳሰል መሞኮራቸው ነው። ከዚህ ውጭ ግን ሁሉም ሊያውቀው የሚገባው የአማራ ክልል ኮሚቴ አቋቁሞ ከደቡብ ክልል አመራሮች ጋር እንደሰራ እና ፈፃሚዎችም በህግ እንደተጠየቁ እየታወቀ አቶ እውነቱ ደፈጠጠ የማይደፈጥጡት ነገር የላቸውመና የብአዴንና የደቡብ ክልል ባለስልጣናትን ይወርፋሉ። በኔ እምነት ግን ጥፋቱ እንኳ ቢኖር የመጀመሪያው ተጠያቂ የአማራ ክልል ፍትህ ቢሮ ባለስልጣን የነበሩ እነ እውነቱ ደፈጠጠ ናቸው ባይ ነኝ። ምክንያቱም እውነተኛ ለህዝብ ተቆርቋሪ ቢሆኑ ንሮ ፈፀሚዎች በህግ እንዲጠየቁ እና አስፈላጊውን እርምጃ እንዲወሰድባቸው ማስተባበር የሙያዊ ድጋፍ መስጠት ነበረባቸው ባይ ነኝ ግን ስጋቸው እንጂ ህሊናቸው አልነበረማ በወንበሩ። ከዚህ ውጭ ግን በአማራ ክልል አሮሚያ ዞን እና በአፋር አዋሳኝ ወረዳዎች፤ በአፋርና በኦሮሚያ፤ በኦሮሚያና በሶማለያ ክልል እንደዚሁ እኮ በግጦሽ እና በውሀ ምክንያት ጊዚያዊ ግጭቶች ይከሰታሉ። የተከሰቱ ችግሮችም አመራሩ በየወቅቱ ሌት ተቀን ብሎ ከሀገር ሽማግሌዎች ጋር በመሆን ይፈታል ነገር ግን እነ እውነቱ ደፈጠጠ ምናልባት በተደጋጋሚ እንደተባሉት ስጋቸው እንጂ ነብሳቸው በወንበሩ ላይ ስላልነበረ አላወቁት ካልሆነ በስተቀር።

በመጨረሻ ላሳስብዎት የምፈልገው የውሸት መረጃ መስጠት እና አንዲት ነገር በፃፉ ቁጥር የህወሐት መሪዎችን ስም ማንሳት ይቅርብዎ ምክንያቱም እርስዎ እንደሚያስቡት የታላላቆቹ መሪዎች ስም ማወቅ ነባር ታጋይነት አያሰጥም፤ የሆነ ያልሆነ በየመድረኩ መዘላበድም ደፋርነት እና አዋቂነትን አያሳይም፤ ይልቁንም ባዶነትን እና ግልብነትን እና አናርኪስትነትን እንጂ ።

እንግዲህ ሀሳቤን ለማጠቃል ባለፈው በፃፍኩት ሂስ አዘል መልስ ይረሙ የገደል መንገድ ይቅርብዎ ብልም አልስሙኝም አሁንም ሀሳብ የሚያጥረው ሰው የግለሰቦችን ስም በማጠልሸት ጊዜውን ይገፋል፤ በሚል ርእስ በፃፉት መልስ እኔ ሀሳብ ስላጠረኝ የእርስዎን ስም ማጠልሸት እንደመረጥኩኝ አስመስለው ፃፉ! ሆኖም እንደልማድዎ የተሰጠዎትን ሂስ ለመመለስ ሲሞክሩ አሁንም የውሸት ቃላት

በሚዘረዝረው ፅሁፎዎ የኔን ሀሳብ የሚያጠናክር ይዘው ብቅ ብሏል፡፡ አስቲ ቃል በቃል ያሉትን ለመመልከት ይችንን ፅሁፏቻን እንመልከት፤

--------ከ 1993 ዓ.ም ጀምሮ ብቻ ሳይሆን ከዛም በፊት የህወሀት የበላይነት በተግባር እየተስተዋለ ስለነበረ በጊዜ ሊታረም ይገባል የሚል እምነት ነበረኝ፡፡ ይህንን ሀቅ እናንተም በተሀድሶ ግምገማችሁ እንዳረጋገጣችሁት የህወሀት የበላይነት ቁልጭ ብሎ ይታይ እንደነበር ይህም ሁኔታ በእህት ድርጅቶች ሳይቀር ቅሬታ ፈጥሮ እንደነበር ግልጽ ነው፡፡ በምሳሌ እንዳስደግፈው ካስፈለገም ታጋይ ካህሳይም ሆኑ ሌሎቹ ተቺዎች ዘንግተውት ወይም የተረሳ መስሏቸው ካልሆነ በስተቀር በጊዜው የህወሀት የበላይነት እንደነበረ የህወሀት ካድሬዎችና ከፍተኛ አመራሩ ጭምር በምሳሌ አስደግፈው ሲገመግሙ የኢህአዴግ ጽ/ቤት እኮ ኢህአዴግን ሳይሆን የህወሀት ጽ/ቤትን ነው የሚመስለው፡፡ ይኸ ብቻ ሳይሆን አንዳንድ የፌዴራል መስሪያ ቤቶች ደግሞ (በዋናነት የመከላከያ፣ የውጭ ጉዳይ፣ የደህንነት) መቀሌ ከተማ ውስጥ የሚገኙ የትግራይ ክልል ቢሮዎች እስኪመስሉ ድረስ በህወሀት አባላትና በትግራይ ተወላጆች ተሞልተዋል በማለት ጭምር አረጋግጠ ትንሽ ቆይተው የተወሰኑት ቀስ በቀስ ወደ አዲስ አበባ እንዲመለሱ ቢደረግም የአሁኑን ሚኒስትር ደብረጽዮን ገ/ሚካኤልንና ዋና ዳይሬክተር ዘርአይ አስገዶምን ጨምሮ በርካታ የህወሀት ካድሬዎችና ከፍተኛ አመራሮች ወደ ትግራይ ብሔራዊ ክልል ሄደው በየደረጃው ተመድበው እንዲሰሩ መደረጉ ይታወቃል፡፡--------

እንግዲህ ማንም እንደሚያውቀው በመከላከያ፤ በደህንነት፤ በውጭ ጉዳይ አከባቢ እንደተባለው እንደ ሰራዊቱ በማመጣጠን ስም በአንድ ጊዜ ማባረር ስላልተቻለ እና ልምድም ስለሚጠይቅ የህወሐት ሰው ይበዛ እንደነበር የማይካድ ሀቅ ነው ምክንያቱም እነዚህ መዋቅሮች በትጥቅ ትግሉ ጊዜም ቢሆን ከህወሐት ውጭ የደህንነትና የውጭ ጉዳይ ባለሙያ የነበረ አይመስለኝም፤ መከላከያም በ 1987 ዓ.ም 30000 ተቀንሶም 47% የህወሐት ሰራዊት ነበር በሂደት ግን እየተተካ ሄዶ አሁን ላይ ከ 17% በታች ደርሷል፡፡ ምናልባት እርስዎ ሁሉም አዋቂ ስለሆኑ ሊነግሩን ይችላሉ፡፡ ሌላው ግን እነ ደ/ር ደብረፅዮን ይሁን እነ አቶ ዘርአይ ወደ ትግራይ የሄዱት እርስዎ እንዳሉት ለማመጣጠን ተብሎ ሳይሆን የአስር አመቱን የተሀድሶ ግምገማ ህወሐትን ከፍተኛ ዋጋ አስከፍሎ ያለፈ እና ህዝቡና አባላቱ ላይ ከፍተኛ ቅሬታና ግርታ ተፈጥሮ ስለነበር የተሀድሶውን መንፈስ እና አላማ ለህዝቡ ለማስረፅና የትግራይ ህዝብም ጥላችሁን ጠፋችሁ እያለ በተደጋጋሚ በመጠየቁ ነበር በርካታ የህወሐት መሪዎች ወደ ትግራይ የተመለሱት በእርግጥ እርስዎ የጠቀሷቸው መሪዎች ምናልባት ለስራ ከባህርዳር ወደ አዲስ አበባ ሲመጡ አቋራጭ መንገድ ፍለጋ ደቡብ ትግራይ አድርገው ሲሄዱ እግረመንገድ አይተዋቸው ይሆናል እንጂ በየዞኑ በርካታ ነባር መሪዎች ተመድበው ሰርቷል፡፡ የተመደቡበት ተልእኮ ሲጨርሱ ደግሞ ወደ የሚመጥናቸው ቦታ ተመድቧል፡፡ በእርግጥ የእነዚህ መሪዎች መመለስ ቅር ያሰኝዎት ነገር እንዳለ ያስታውቅቦታል ምክንያቱም እርስዎ እዚህ እያሉ እንዴት እነሱ መጥተው እንደተመደቡ ግራ የተጋቡ ይመስላሉ፡፡

ለማንኛውም አሁንም በያዙት መንገድ ገደል ካልሆነ በስተቀር ስልጣን አያስገኝም፤ እርስዎ አዲስአበባ ቢመሽጉም በክልል ያሉ ጓደኞችዎ መግብያ መውጫ አጥቷል ምክንያቱም ውሀ እና አመፅ ሲወስድ እያሳሳቀ ነው አሉ፡፡ የትግራይ ሰዎችንን ማንገላታትና ማሰቃየት ሲጀመር ህወሐት ያዳከማችሁ መሰላችሁና በርቱ እያላችሁ በየፌስ ብኩ እና በሌላውም እየፀፋችሁ አመፁን ደገፋችሁ፡፡ በእርግጥ ሁሉም ሊገነዘብ የሚገባው የቅብብሎሹ ዱላ ያልጣሉት ግን በፅናት ታግሏል፤ ይህ እሳት የበለጠ የሚጎዳው እኛን ነው ብሎው በድፍረት ታግሏል፤ በህወሐት ሳንባ የሚተነፍሱ እየተባሉም ጭምር በፅናት ታግሏል፤ጉዳትም ደርሶባቸዋል፡፡ እነ መርህ አልባው እውነቱ ደፈጠጠ ደግሞ ሰላማዊ ስልፉ ወደ አማራ ክልል ጎንደርና ባህርዳር ተሻግሯል አሉን፡፡

ለማንኛውም እነ እውነቱ ደፈጠጠ ጉዳቱ ስላልደረሰባችሁ፤ በትጥቅ ትግሉም ይህ ነው የሚባል እንግልት ሳይደርስባችሁ ለትልቅ ቦታ ስለደረሳችሁ የጉዳቱ መጠን አትገነዘቡትም፡፡ በእርግጥ መርሁን የተረዱ በቅርብ ጊዜ ወደ ድርጅቱ የተቀላቀሉትም ጭምር ማንም ሊገምነተው ከሚገባው በላይ ታግሏል እንደዚህ አይነቶቹ ትክክለኛ የዱላው ተቀባዮች ናቸው፡፡ እነ እውነቱ ደፈጠጠ ያሳሳቷቸው ደግሞበርካታ መሆናቸው እሙን ነው ይህ እንግዲህ እየተካሄዱ ባሉት የተሀድሶ መድረኮችም የተረጋገጡና ምን ያል የቁልቁለት መንገድ እየተጓዙ እንደነበር ተገንዝበው አሁን በቁርጠኝነት ክልላቸውና ሀገራቸውን ለመካስ እየተንቀሳቀሱ ነው፡፡ አሁን ችግር የሚሆነው ሁሉን አወቅን ባዮች ግን ደግሞ በተግባር ባዶ የሆኑትን የተሀድሶው ፀበል የማይደራሳቸውን እነእውነቱ አይነቱ ነው፡፡ ለማንኛውም እንደዚህ አይነቶቹ ሰዎች ከስህተታቸው ካልተማሩ የሚታረሙበት ቦታ ይታወቃል እና በቃ ሊባሉ ይገባል ባይ ነኝ፡፡

እነ እውነቱ ደፈጠጠም እስከ አሁን የበደሉትን ህዝብ ለመካስ እንዲሁም በህዝቡ የደረሰው ስቃይና በደል ተሰምቷቸው የሚፀፀቱበትና የሚክሱበት ሁኔታ እንዲፈጠር ምኞታችን ነው፡፡

መልካሙን ያሰማን፡፡